# ቃለ አጋኖ ፖለቲካና መዘዙ

ውብሸት ሰለሞን

*ቃል--ወሬ ከሆነ ይሙት*
*ሥራ ግብር ካልሆነ*
*ይሙት::*
*(ፈቃደ አዘዘ )*

*( ከዚህ በፊት ይህን ቃለ አጋኖ ፖሊተካ የሚለውን ሌላ ሰው ተጠቅሞበታል ስለተባልኩ ፀሀፊው ንሳላስፈቅድ በመውሰዴ ይቅርታ እጠይቃለሁ)*

*ወደ ፅሁፌ ቁም ነገር ከመግባቴ በፊት ወንድም ጌታቸው ረዳ በእንግሊዝኛ በሰሞኑ ያበጠው ይፈንዳ ብሎ ደፍሮ ወይዘሪት ብርቱካንን--እንኳን ተፈታች ደስ አለን ካለ በኋላ-- በድከመቷ ወገናዊ ወቀሳ ሊያቀርብ መሞከሩ የልብ የልብ ሰጠኝ ብል ሀሰት አይሆንብኝም:: እኔም እንደ ወንድሜ የፖለቲካ መሪዎች አለምንም ምህረት መገምገም አላባቸው ባይ ነኝ:: ብርቱካንንም ሆነ አቶ ኃይሉን፤ ዶክተር ብርሃኑን፤ ፕሮፌሰር መስፍንን ሆነ ኢሕአፓዎችን ማን ነክቷቸው ብለው ሊያፍኑን ከሚነሱት ጋር መሰረታዊ ልዩነትና ክብደት ያለው ቅራኔ ሊኖረን ይገባል::*

*የሀገራችን ፖለቲካ ከደርጉ የበሸቀጠ ዘመን ጀምሮ እየተበላሸና ንቃት በጥራዝ ነጠቅነት እየተተካ ፖለቲከኞችም ዝቅጠት እያጠቃቸውና የፖለቲካ ብስለታቸውም አነጋጋሪ እየሆነ መምጣቱ የሚ ታወቅ ነው:: በታሪክ እንዳየነው ደግሞ እያንዳንዱ የተበላሸ ስርዓት ወይም አገዛዝ በባሰው እየተ ተካ የሕዝብን ሰቆቃ አባብሷል:: በሀገራችን የአፄ ኃይለሥላሴ አገዛዝ በባሰው ደርግ ተተክቷል፤፤ ይህም መጥፎ ስርዓት ለከፋው ወያኔ በር ከፍቶ መሰረት ጥሎ አልፏል:: የእንግሊዝ ሌበር ፓርቲ መንቀዝ ለታቸር አመችቷል:: የኢራኑ አምባገነን ሻህ ለአያቶላዎቹ ድልዳል ጥሏል:: የአልጄሪያ አገዛዝ መበላሸቱ ለአክራሪ እስላሞች በር ከፍቷል:: ጎሰኛው ዚያድ ባሬ ለጦር አበጋዞች ረብሻና ሶማሊያ ዛሬ ላለችበተ ቀውጢም ዳርጓታል:: ፓኪስታን፤ ህንድ ወዘተ ተመሳሳይ ሁኔታዎች ታይተዋል:: ሁኔታው ለፖለቲካ ጥራት አመቺ አልሆንም ቢባል ተገቢ ነው:: በዓለም አቀፍ ደረጃ ም የ " አገዛዝ" ሶሻሊዝም በመፈራረሱና የካፒታሊዝም ዋና ተከላካይና አራማጅ አሜሪካ ብቸኛ ኃያል መንግሥት ሆኖ መሰየሙ በዓለም ሁኔታ ላይ የተደነጋጋረ ሁኔታን አስፍኗል:: በዚህ ሁሉ የተነሳና ከዚህም ተያይዞ የኢትዮጵያ የፖለቲካ መስክ በአያሌ ውዥንብር የተጠቃ ሆኖ ይገኛል:: የዚህም ምልከት ናቸው ብዬ በበኩሌ የማቀርባቸው ክስተቶች የሚከተሉት ናቸው፤*

- *ፖለቲካ በምዕራባውያን ፍሪ ፎር አል እንደሚባለው ሁሉም ገብቶ የሚቧርቅበት መስክ መሆኑ፤*
- *ፖለቲካው ብሰለትና ጥራት የሌላቸወ ምሁሮች ዋና የፖለቲካ ሰባኪ ነን ብለው መነሳታቸ ው፤*
- *በፖለቲካ አቅዋም ዙሪያ ጤናማ ውይይት/ክርክር ወይም የሀሳብ ፍጭት ሊደረግ ባለመቻ ሉና ሂስና ትችትም የሚያስወግዝ ሆኖ በመገኘቱ፤*

- የፖለቲካ መሪነት ሚና ለቦታው ዝግጁ ላልሆኑና ብቃቱም ለሌላቸው ወይም ለድብቅ የወያኔ ተጓዳኞች በመስጠቱ፤
- ካለፈ ተመክሮ ለመማር ዝግጁነት በመጥፋቱና ጠላትና ወዳጅንም መለየት ማቃቱና
- በመጨረሻ ቢቀርብም ዋናነት ያለው ደግሞ ትግል መሰዋዕትነትን መጠየቁን አለመቀበል

በሚል አቀርባቸዋለሁ::

" *ዛሬም የዘመንን ጥያቄ ሳልመለሱ*
*አእምሯቸውን ሳልፈተኑ*
*እንደዋጡት ለሚያውጡ*
*እውቀትን ከሀገር ፍላጎት*
*ከእውነታዋ ላላጣቀሱ ::*
*ይቅርታ!!!!"*
*(ፈቃደ አዘዘ )*

በይቅርታ እንጀምርና ወይዘሪት ብርቱካንንም ሆኑ ሌሎችን ደፈራችሁ አንባልና ወደ ተነሳሁበት ቁም ነገር ስመለስ ቃለ አጋኖ ፖለቲካ መዘዙ በዝቶ አቅጣጫ እያሳተን ብቻ ሳይሆን እርስ በርስም እያናከሰን ነው:: ከዚህ ቀደም ለዚህ የተሰጠው ትርጉም ምን እንደሆነ ባላስታወስም የኔ ቃለ አጋኖ ፖለቲካ በጫጫታ ለግለሰቦች የሚሰጡ ና የሚዘፈኑ ሙገሳዎችንና ግምቶችን ይመለከታል :: ወንድም ጌታቸው እንዳለው ብርቱካንን ከኢየሱስና ማንዴላ ማመሳሰል እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ የሚችል ነው:: ከዚህ ቀደም በአፍሪካ ቀንድ መፅሔት አንድ ፀሃፊ ፕሮፌሰር አሥራትን ማንዴላ ፤ኢየሱስና ጋንዲ ተጣምረው ማለት ናቸው ብሎ አቅርቦ ነበር:: ወደ ሰዎቹ እንመለሰብታለን ግን ሰውን ከኢየሱሱ ማመሳሰል ከጥፋትም በላይ ኃጢያት ሊሆን መቻሉን መሳት ባልተገባ ነበር:: ከዚህ ቀደም ምንም የፖለቲካ ተመክሮ የሌላቸው ቢሆኑም ወይም--ይባስ ብሎ--የነበራቸው ተመክሮ አሉታዊ (ማለትም በጨፍጫፊው መንግሥቱ ስር በካድሬነት ወይም ኢሠፓ መሪነት ያገለገሉ' ወይም የወያኔ አመራር ኮሚቴዎች አባል የነበሩ) የነበረ ቢሆንም ገና ወደ ሕዝብ ጎራ ጠጋ ጠጋ ሊሉ ሲነሱ በቃለ አጋኖ ወገባቸው ይጎብጣል:: ለማለት ያህል ብዬ እንጂ መጉበጥ ሳይሆን ልባቸው ይደነድናል፤ ይታበያሉም፤ ማን ተናግሮን፤ ካባ አልብሱን ስገዱልንን ያመጣሉ:: ተከታዮች ነን ብለው ውዳሴ ከንቱ የሚያደርጉት ክፍሎች አንድም ንቃት አንሷቸው የተደናገሩ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በግርግር እበላባይነታቸውን ሊያስከብሩ ወይም የራሳቸውንም ወንጀል ሊሸፋፍኑ የሚሞክሩ ናቸው:: ለምሳሌ ዛሬ አክራሪ አነግ ነን ባዮች አክራሪ የደርግ ሎሌዎች ነበሩ :: የኦሕዴድ አልማዝ መኮና ሐሰን አሊ (የአርባጉጉ ሕዝብ አራጅ) ዛሬ የት ናቸው? የተቃዋሚ ድርጅቶች ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የሆኑ ስንት ቀንደኛ ደርጎች አሉስ አይደል? ዛሬ የሚሞገሱ፤ ታጋይ፤ ሀገር ወዳድ፤ ጀግና የሚባሉ? ወይዘሪት ብርቱካን የትግል ተመክሮዋ አነስተኛ ቢሆንም

ታሪኳ ደግሞ የደርግም የወያኔም ሚኒስቴር ወይ ምክትል ሚኒሰቴር ነበረች አይልም፡፡ የሌሎቹን ግን የምናውቀው ነው፡፡

ገና ሳይፈተኑ ወይም ተመክሮአቸው ይቅርታን ከሕዝብና ጥንቃቄንም የሚያስጠይቅ ሆኖ ሳለ ከእንጭጩ ማንዴላ፤ ጋንዲ፤አዋቂ ታላቅ መሪ፤ ጄኔራል ኮማንደር፤ ብርሃን ለጋሽ ፕሮፌሰር፤ አንግ ሱን ኪ ወዘተ እየተባሉ ይሞገሱና ነገሮች ሁሉ ሚዛንና ልክ-ለከት ያጣሉ፡፡ ሁሉም ግለሰብ የራሱ አሻራና ጠረን ያለው ሆኖ ሳለ በሌላ ሰው መልክና ቁመና ሊገለፅ መሞከሩ አግባብ ያለው አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ጀግና ወይም አርበኛ መባሉ ሲገባ የኢትዮጵያን ማንዴላ የሚለውን ስያሜ --ያውም ወር ታስሮ ለመለቀቅ የወያኔ ጮሌ-- መስጠቱ በራስና በትግል ላይ መቀለድ ሆኗል ፡፡ ልደቱ የተባለው አፈ ጮሌ ካድሬ --ያውም በታቦት ስርቆትና መአሕድን በማፍረስ ሲከሰስ የነበረ-- ማንዴላ ብሎ መጮሁና ይህ ግለሰብ የወያኔ መሳሪያ ነው ሲባል አለመስማቱና ሀቁን የተናገሩትን ማውገዙ ምንኛ ብዙዎች ይህን ዓይነት ሰዎች ከሕዝብ ጎራ መራቅ እንዳለባቸው የሚጠቁም ነው፡፡ ከዚህ በተጫማሪ አንድን ግለሰብ በራሱ ስራ፤ተግባር፤ ሚናና አስተዋፅዖ እንዲሁም ማንነት ማድነቅ ሲገባ ሌላ ማንነትን --ያውም የማይስማማን--መለጠፉ ስህተት ነው፡፡ የባንግላዴሽ ደራሲ ሆና አክራሪ እስልምናን በመተቸቷ ከሀገሯ የተባረረችውን ታስሊማ ናስሪንን “ የባንግላዴሽ ሳልማን ራሽዲ ” ባሏት ጊዜ ራሽዲ ግልፅ ደብዳቤ ፅፎ ይቅርታ ጠይቋታል፡፡ ያንቺን ማንነት፤ታሪክሽን፤ ተጨባጭ ሚናሽን የኔን ስም በትከሻሽ ላይ በመጫን ሊያደበዝዙት ሞክረዋልና ይቅር በዪኝ ብሏታል፡፡ ብርቱካንን በሚናዋ ማድነቅ ሲገባ የኢትዮጵያ ማንዴላና አንግ ሱን ኪ ነሽ ማለቱ የራሷን ማንነት ሰራዡ ከመሆኑ ሌላ የእሷ ተመክሮና የተጠቀሱት ማንዴላና የበርማዋ ታጋይ ታሪክና ሚና ከቶም የሚገናኝ አይደለም፡፡ ሁሌም የባዕድ መሪዎችን ስም ለመጥራትና በእኛዎቹ ላይ ለመለጠፍ መነሳቱ  የዝቅተኛ ነት ስሜትንም አንፀባራቂ ነው፡፡ አልፎ ተርፎ ግን ማንንም ግለሰብ ኢዩሱስ ክርስቶስ ጋር ማመሳሰል ብልግናም ሐጢያትም ነው፡፡ መረን  የለቀቀ ውዳሴ የሚያሰሙና ተክለ ሰውነትን  በአፀያፊ መንገድ ሊያስፋፉ የሚሞክሩ ግለሰቦች ሚናቸው በሚገባ መመርመር እንዳለበትም ተመክሮ ይነግረናል፡፡

ጫንቃው ደካማ የሆነ ፍጡር ላይ የክርሰቶስን ግማደ መስቀል ለመጫን መሞከር ውሎ አድሮ ያጋልጣል፡፡ ዛሬ አፈርን አይሉም እንጂ ልደቱ ክህደቱን መሪያችሁ ነው ብለው ሊጭኑብን የጣሩት ሁሉ ይቅርታ ሊጠይቁን ይገባል፡፡  ልደቱ አለሚናውና አቅሙ የተሰጠው ማንዴላዊ ስም ብዙዎችን አደናግሮ ኋላም ልደቱ ከህዲነቱ ሲገለፅ ወደ ቀቢፀ ተስፋ ሰዷቸዋል፡፡ የወያኔ ምክትል ሚኒሰቴር የነበረውና የጎተ ድርጅት መስርቶ ሊበላ ቋምጦ የነበረው በየነ ጴጥሮስም የተቃዋሚ መሪ ተብሎ የብዙ ድርጅቶች ህብረትንም መሪ የብሎ ነበር፡፡ ታሪክ ተረስቶ? እኔና ሌሎች አሁንም ቢሆን የተሰጠ ምክንያት ቢሰጥ ከነገደ ጎበዜ ጋር ህብረት ትክክል አይደለም ባይ ነን፡፡ የነስዬና  ገብሩ አሰራትማ አይነሳ! ይህ በዚሁ ይቅርና ግን አላግባብ መሪ የተባሉትንም ማሞገስ ወይም ገና ያልተፈተኑትንና ተመክሮአቸው ያልተጠናከረውን ሰማይ ሰቅሎ ማንዴላ ጋንዲ ወዘተ ብሎ ማወደስ ትግላችንን ጎድቷል፡፡ ታሪካቸው መጥፎ የነበረ በሆነበት ሲሰጣቸው የቆየው ወዳሴና ስያሜ

መደረግ አልነበረበትም:: ወይዘሪት ብርቱካን ዓይነቶቹን በተመለከተ ወጣትነቷ፣ ሴትነቷ፣  አርአ ያ ልትሆንና ልታሰባስብ መቻሏ ወዘተ ሊደነቅና በርቺልን የሚያሰኝ ቢሆንም የተጫነባት ቅፅልና ስያሜ ክምር ግን አጓጉል ጫና ሆኖባታል፡፡ ዛሬ ከእስር ስትፈታ ለምንስ ምህረት ከመለስ ዜናዊ ጠየቀች በሚል ህፍረት እየተሰማቸው ያሉትና ይህንንም ለመደበቅ በሚያስገርሙ ፅሁፎች አማካ ይነት መጣር ላይ ያሉት ሁሉ የራሳቸው የተሳሳት ግምት ሰለባና የውዳሴያቸውም ተጠቂ መሆና ቸው እየታየ ነው:: በቅድሚያ ብርቱካን ይቅርታ መጠየቋ ከማንም በፊት ቅሌታም የሚያደርገ ው መለስና አገዛዙን ነው:: በብርቱካን ላይ ከባድ ጫና መደረጉና ከበውም እንዳወከቧት ጥርጣሬ የለውም:: ስለዚህም ፈርሙልኝ እያለ እስረኞችን ማስጨነቅና በእሱም ቤትና ግምት ማዋረድ የለመደው መለስ ነው እንደገና መወገዝ የሚገባው:: ይህ ሀቅ ቢሆንም በሌላው በኩል ደግሞ ተጨፈኑ ላሞኛችሁ ዓይነት መለስ ድል ተመታ፣ ሶቅራጥስ፣ ክርሰቶስና ብርቱካንና ወዘተ ብሎ ድንግርግር መፍጠሩና ራስን ለትዝብት መዳረጉ አስፈላጊም ጠቃሚም አይደለም:: ወይዘሪት ብርቱካን የሚጠበቀውን ፅናት አላሳየችም ማለትም ስድብ ሳይሆን ያለውን ሁኔታ በሚገባ መገም ግም ነው:: እሷንም ዝቅ የሚያደርግ አይደለም:: ቅዱስ ነኝ፣ እንከን የማይወጣልኝ መሪ ነኝ፣ ማንዴላ ነኝ ብላም ሰለማታወቅ እሷ ቋምትጠይቀበት መሰረት የለም:: በእሷ ላይ ያልሆኑ ስሞችን ና ግምቶችን የለጠፉ ናቸው ተጠያቂ፣ የሚሳፍርም ካለ ማፈር የሚገባቸው:: ብርቱካን ምህረት የጠየቀችው ከጎኗ አልቆም ብለን ነው ብሎ አንድ ግለሰብ የፃፈው ደግሞ ከሀቅ የራቀ ማስተዛዘኛ  ነው:: ብዙሃኑ ብርቱካን ትፈታ ብሎ ተንቀሳቅሷል፣ከጎኗም ቆሟል፡፡ የነ አበራሽ በርታን ሰም የማያነሱት አምኔስቲና ህዩማን ራይትስ ዋች ሳይቀሩ የአሜሪካንን ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጨምሮ--ጮኸውላታል::

መታሰርና ጨለማ ቤት መግባት ከተነሳም ይህ ሁሉ በወይዘሪት ብርቱካን የተጀመረ አይደለም:: ብዙዎች እስርን ቀምሰናል፣ አልፎም ተደብድብናል:: ያለፈው ይቅርና፣ የወያኔ አገዛዝ ምህረት ጠይቁኝ ሲል እምቢ ብለው ደብዛቸው የጠፋውን እንተውና፣ ተታኩሰው የተሰዉትንም እናንሳና ጀግናው ዶክተር ታዬ ወልደ ሰማያት ራሱ በቂ ምስክር ነው::   በሰንሰለት ታስሯል፣ ታፍኗል፣ ጨለማ ቤት ተወርውሯል፣ብዙ ስቃይ ደርሶበታል ግን ከወያኔ ምህረትን አልጠየቀም:: ስለዚህ ፅናትና በቃትን ከሕዝብ ትግል አንፃር ስናነሳ ማነፃፀራችን የግድ ይሆናል:: ገበያ ባልወጣሽ ሲል ሐበሻ እንደሚተቸው ሁሉ ባዕዳንም እሳት ሙቀት ከጠላህ ኩችና/ወጥ ቤት አትግባ ይላሉ:: ዛሬ በኢትዮጵያ ፀረ ወያኔ ትግል የሚገቡና ከዚያም አልፎ የሕዝብ ትግል መሪ ነን የሚሉ የሚጠበቅ ባቸው ፅናት ቀላል አይደለም:: ቃሌን አክብሪያለሁ ማለትም ይጠበቅባቸዋል:: መሰዋዕትነትን ይጠይቃል--ልጄ እናቴ የሚለው ሊቀድም አይችልም:: ጨካኝ ቢመስልም ይህ ነው የትግል ይዘት:: አንድ ለናቱዎች ናቸው ደረታቸውን ለጥይት የሰጡ:: እነ አሰፋ ማሩና ተስፋዬ ታደሰም ልጆች ነበሯቸው:: እኔና መሰሎቼ ወይዘሪት ብርቱካን አንኳን ተፈታች ስንል መታሰሯ ከመጀመ ሪያውም ህገ ወጥ በመሆኑና ከዚያም የእሷ አቅሟና ልኳ ይህ ከሆነ ላረገችው አመስግኖ መቀጠል ያስፈልጋል ከሚል ነው:: መሆን የማትችለውን ካልሆንሽ ብሎ ማሰቸገርም ተገቢ አይሆንም::

ትግሉ ግን እሷ ካሳየችው ፅናት በላይ ጠያቂ ነው፡፡ ብርቱካን ማንዴላ ናት ብለን ከመጀመሪያው ያላመንን ደግሞ ምህረት ጠየቀች ብለን አንሸበርም፤ አናፍርም፡፡ የአቅሟን ታግላለች--ለዚሁም ምስጋና ባትፈልግም ተመስገኚ ልንላት ይገባል፡፡ ነገ ግን ትግሉ ሌሎች መሪዎችን፤ ብቃትና ጥራት ያላቸውን ድርጅቶችን ይጠየቃል፡፡ መሪያቸው ተይዛ ምርጫ የሚገቡና እርስ በርሳቸው ተናክሰው መሳቂያ የሚሆኑ የሚከፋፈሉትን አይፈልጋቸውም፡፡ አዲስ ምዕራፍ-- ስለዚህም ውዳሴ ከንቱዎች ሊበሳጩ ቢችሉም ኢትዮጵያ ብርቱካንን ዓይነት መሪ ትጠብቃለች ማለት ከባድ ስህተት ነው፡፡ ለዚህም ነው ራሳቸውን ፕሮፌሰር አል ማርያም የሚሉት ምሁር ብርቱካንና የምህረት ጥየቃን ክስተት በአንድ እንዳታነሱ ብለው የፃፉት አፈናና ማስፈራሪያ መስሎ የሚታየኝ፡፡ የፃፉት የሚከተለውን ነው

***For the rest of us who love, admire and respect Birtukan, let us resolve from this day on never to mention the name Birtukan Midekssa with the word "pardon" in the same phrase or sentence. It is blasphemy to say Ethiopia's First Daughter and foremost patriot was pardoned into freedom by a universally-condemned human rights abuser.[***

ብርቱካንን ብናከብራትም ከዚህ ባሻገር ከግለሰብ ስሜት ባለፈና በበለጠ ደረጃ የህገርና የሕዝብ ደህንነትና ከወያኔ የመላቀቅ ጉዳይ አለና ብርቱካን ስንል መታሰሯን፤ ምህረት መጠየቋንና መለስ ም ምህረት መስጠቱንና በዚሁም መመፃደቁን የማናነሳበት ምክንያት የለም፡፡ ለምንስ አይነሳም? የሚያሳፍር ከሆነ በጋራ እንፈርበት፡፡ ስህተት ተፈፅሞ ከሆነ እንማርበት፡፡ ለነገሩማ ከዚያም በፊት ቢሆን የቅንጅት መሪዎች በመሳ ምህረት መጠየቅ አልነበረባቸውም፡፡ ኢንጅኔር ሀይሉስ ከምርጫ ው በፊት የስነ ምግባር ሰነድ ተፈራረሙ ተብለው ሲወቀሩ አልነበረምን? ወይዘሪት ብርቱካን ምህረት ጠየቀች አትበሉ የሚሉን ምህረት በመጠየቋ እያፈሩ ያሉ ናቸው--አላፈርንም ቢሉም፡፡ በመሰረቱ የሚያሳፍር ጉዳይ የለም--ማፈር ያለበት መለስ ዜናዊ ነውና፡፡ ማፈር የመጠባቸው ግን ብርቱካን ማንዴላም ሌላም ናት ብለው የለፈፉትና አሁንም ያንኑ ሊያሳምኑን የሚጥሩት ናቸው፡ ቃለ አጋኖ ፖለቲካ ወይዘሪት ብርቱካንን ካልሆነ ፎቅ ሰቅሎ የእሷንም ህይወት፤ የሁላችንንም ትግል ጎዳ፡፡ ስለዚህም መታረሚያ ጊዜ መጥቷል--መሸፋፈን ሳይሆን እቅጩን ተናግሮ በመሸበት ማደር፡፡ ለዚህም ነው ወንድሜ ጌታቸው ረዳን የማመሰግነው፡፡ የኢትዮጵያ ትግል መሪ ነን ብለው ኦነግ ሊተባባር ነው እርስ በርሱ ብለው ጮቤ የሚረግጡትን የዋሆች (ሌላ ተገቢ ቃል ላለመጠቀ ም) ላይ የሰነዘረውም ወቀሳ ያስደሰተኝ ለዚህ ነው፡፡

ፍሬ ሞቶ ነው የሚያፈራ በሚለው ግጥማቸው መምህር ፈቃደ አዘዘ የሚከተለውን አስፍረዋል፤

*" እውነት ማለት "ህይል" ከሆነ ፤ህይል ከሆነ ልኩ*

*እኛ ሞትን አንሸሽም አርበኝነት ነው ምሱ!*

*አለንና ምክንያት ለትግላቸን ዓላማ*

*የማይገደብ ጎርፍ ጉልበት እንዳየር የተንሰራፋ*

*አለንና በየልባችን እምነትና አቅጣጫ*

*ቆራጥነተን ጨምሮ እንደ ፀሐይ የሚመራ*

*ቃል ይሁን ዛሬም ዳግመኛ መግደልን ሳንፈራ*

*እስከዛሬ የሞትንለትን ነፃነትን ሳናፈራ:: "*

*ይህ ነው ቋንቋው:: በሰላማዊ ትግል ወይም በህይማኖትና እምነት ሽፋን የሚሰበከው ሁሉን አቀፍ ፍቅርና መተቃቀፍ-ወይም መማማር-- በተጨባጩ ምንም ቦታ ወይም ፍቱንነት የለውም:: መለስ የሚገዛው እየገደለ ነው:: መለስን ከነአገዛዙ ሊያስወግዱ የሚነሱ ደግሞ ቆራጥና ፅኑ ከመሆን ባሻገር ጠላትንም ለመግደል የተዘጋጁ መሆን አለባቸው:: እስካሁን ባየነው መሪ ነን ብለው ቦታ የያዙት ብዙዎቹ የትግሉን መመዘኛ ፈተና አያልፉም:: ከዚህ አንፃር ነው የመለስ ዜናዊ የመህረት ጨዋታ በግምት የምናስገባው::*

*ወይዘሪት ብርቱካን እንኳን መከራሽ ለጊዜውም ቢሆን አክትሞ ለቤትሽ አበቃሽ:: ሁኔታው ካመቸሽ ሳልተፈቱትም የምትጮኺ ብትሆኚ ደስ ይላል:: ጊዜ ወስጂ ሁኔታውን እገመግማለሁ ያልሺውም ደግ ነው--ያስፈልጋል::*

*ቃለ አጋኖዎች ደግሞ ታቀቡ:: ሀቀን አትሸፋፍኑ::ሕዝብንም አትናቁ:: በመለስ እርምጃ ሞራላች ሁም አይድቀቅ:: ሽንፈት ድል ደልም ሽንፈት አይሁንባችሁ:: ጊዜ ወስዳችሁ ሁኔታውን ለማጤ ን ሞክሩ:: የሕዝባችን ትግል ባለፉት ዓመታት ባሰፈናችሁተ የተሳሳት ጎዳናና ጩኸት መሰረት ተበላሽቶ የሚቀጥል ወይም የሚደናቀፍ አይሆንም::*

*ወንድም ጌታቸው እንዳለው እኔም ያው ውግዘታችሁንና ስድባችሁን ብታወርዱብኝ ወይ ፍንክች የአባ ቢላዋ ልጅ ባይ ነኝ:: ወያኔ የበላይነትን ሲይዝ ማወቅና ይህንንም ለማክተም መጣር እንጂ ሽንፈትን ድል ማለቱ የሰጎን ፖለቲካ ነው:: ጎጂ:: የኢትዮጵያ ጀግና ልጆች ሞልተዋል፤ የፅናት አርአያዎች፤ሞት አይፈሬዎች:: ማንዴላ መባልንም አይፈልጉም፤ ክርስቶስ በሉን ብለውም ፀያፍ ቅብጠትን ሊሰሙ ፍቃደኛ አይደሉም:: ታጋይ መባልን ይመርጣሉ:: ፅኑና ቆራጥ መባልን በገቢ ር ማስመስከር ይወዳሉ:: የጀግንነት ቅርሰ አላቸውና ልበ ሙሉ ናቸው:: በሕዝብና በሀገር ያምና ሉናም ሞትን አይፈሩም::*